# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 ፃፍትሕ፣የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 8 ሃምሌ 3 2000 ዓ.ም


አንብበው
ያስነብቡ !
አባዝተው
ያሰራጩ !

## ለሱዳን በተሰጠው መሬት የኢትዮጵያውያኑ ቁጣ እየነደደ ነው፡፡ የሲያትልና ዋሽንግተን የጎንደር ተወላጆች ማህበር ቁጣውን ገለፀ፡፡

ከሑመራ እስከ ጋምቤላ ድረስ ያለውንና ርዝመቱ 1600 ኪሎ ሜትር፤ስፋቱ ደግሞ 50 ኪሎ ሜትር የሆነውን ለም መሬት የአቶ መለስ አገዛዝ በድብቅ ለሱዳን መንግስት በመስጠቱ በአገር ቤትም ሆነ በውጭው ዓለም በኢትዮጵያውያኑ ዘንድ የተቀሰቀሰው ቁጣ እያደር እየጋመ ነው።

በሲያትልና ዋሽንግተን የተቋቋመው የኢትዮ-ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ይህንኑ አስመልክቶ ረቡእ ሰኔ 25 2000 ኢ.ም በርካታ ምሁራን የተሳተፉበት ስብሰባ ዋሽንግተን ላይ ከማድረጉም በላይ፤ በማግስቱ ሀሙስ ሰኔ 26 በወያኔ ኢህአዴግ ኤምባሲ ፊት ለፊትም በርካታ ኢትዮጵያውያን የተሳተፉበት የተቃውሞ ሰልፍ አስተባብሯል፡፡
ይህ በእንዲህ እንዳለ በሲያትልና ዋሽንግተን የጎንደር መረዳጃ ማህበር አባላት በጉዳዩ ዙሪያ ሰሞኑን ያካሄዱትን ታላቅ ስብሰባ ሲያጠናቅቁ ባወጡት ባለ አምስት ነጥብ የአቋም መግለጫ፤ የአቶ መለስ አገዛዝ የፈፀመውን አገራዊ ክህደት አጥብቀው ከማውገዛቸውም ባሻገር ዳር ድንበራቸውን ለማስከበር የህይወት መስዋዕትነትም ቢሆን ለመክፈል ዝግጁ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

"በታሪክ ተወዳዳሪ የማይገኝለትን ይህን ታላቅ ጥፋትና ክህደት አጥብቀን እንቃወማለን፤በቁጭት ብቻም አናልፈውም"ያሉት ኢትዮጵያውያኑ፤ፍፁም ኢትዮጵያዊ ደምና ባህርይ የለውም ያሉትን የመለስ ን አገዛዝ እስከመጨረሻው እንደሚፋረዱት አስታውቀዋል።

## የግንቦት7 ድምጽ ጋዜጣ የተከበሩ አንባቢዎቹን ይቅርታ ይጠይቃል፡፡

በደረሰብን የቴክኒክ ችግሮች የተነሳ የሰኔ 26 2000 ኢ.ም እትም በቀኑ ለማውጣት ባለመቻላችን፣ በጋዜጣው ላይ ተዘጋጅተው የነበሩ ዜናዎች ግዜው ያለፈባቸው ሆኑ፡፡ በእዚህም የተነሳ የሰኔ 26ቱን እትም ለመሰረዝ ተገደናል፡፡ ለእዚህም ውድ አንባቢዎቻችንን ይቅርታ እንጠይቃለን፡፡

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## "ሃገር ሳያጠፉ፣ መለስን እናጥፋ!"

ፕ/ር ዳንኤል ክንዴ
የኢትዮጵያን ሃብት ከመዝረፍ፡ ሕዝቡን ከመጨረስ አልፈዉ በሚስጥር የሃገሪቱዋን መሬት ለባዕዳን አሳልፈው በመስጠት አቶ መለስ ዜናዊ ተወነጀሉ። የኢትዮ-ሱዳን ድንበር ኮሚቴ በዋሽንግተን ዲሲ ማሪዮት ሆቴል ባለፈው ረቡዕ ባዘጋጀው ስብሰባ በርካታ ምሁራን ተገኝተው ምሁራዊ ትንታኔ ያቀረቡ ሲሆን ሁሉም ኢትዮጵያ ልትወጣ በማትችልበት ከፍተኛ ቀውስ መግባትዋን አስገንዝበዋል።

ከተጋባዥ ተናጋሪዎች ውስጥ ፕ/ር ዳንኤል ክንዴ ሲናገሩ ሃገራችን ኢትዮጵያ ከመጥፋትዋ በፊት ተባብረን መለስ ዜናዊን እናጥፋው ብለዋል።
ወደገጽ 2 ዞሯል

## አስራ ሰባት አርቲስቶች አሜሪካን ቀሩ፡ ምኒስትሯ ብቻቸውን አዲስ አበባ ተመለሱ

የኢትዮጵያዊትዋን ድንቅነሽ (ሉሲ) ስደት በአሜሪካን ሃገር ተከትሎ በባህል ስፖርት ሚኒሰትር ዴኤታ የሚመራው የብሄራዊ ትያትር የባህል ሙዚቃ ቡድን በሙሉ አሜሪካ መቅረቱን የግንቦት7 ዜና ዘጋቢ አስታወቀ። ከአስራ ሰባት በላይ አባላትን የያዘው ይህ ቡድን አሜሪካን ሃገር ለመቅረት የወሰነው ኢትዮጵያ አሁን ያለችበት የፖለቲካ፡ የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ሁኔታ አሲጊ ደረጃ መድረሱ እንደሆነም ከአርቲስቶቹ ለመረዳት ተችሏል። የባህል ዘፈኑን በሰሰሜን አሜሪካ ለማሳየት ከገቡት ውስጥ ሁለቱ አውሮፕላን ማረፊያ ላይ እንደደረሱ ሚንስትሯን ጥለው መሮጣቸውንና ስደት መጠየቃቸውንም ለመረዳት ችለናል።በተለያዩ የአሜሪካን ግዛቶች የባህል ዝግጅት ለማቅረብም ተይዞ የነበረው ፕሮግራም በቡድኑ አለመገኘት መሰረዙም ተዘግቧል።የባሕል ምኒስትር ዴኤታዋ ብቻቸውን በየዝግጅቱ ከተዟዟሩ በኋላ ብቻቸውን አዲስ አበባ ተመልሰዋል።

## የግንቦት 7 ታላቁ ስብሰባ በ "ይቻላል"ስሜት ተካሄደ

ግንቦት 7፣በዋሽንግተን ዲሲ ያደረገው ስብሰባ በከፍተኛ መንፈስ መካሄዱን ስብሰባውን ይከታተሉ የነበሩ አስተያት ሰጭዎች ገለጹ፡፡ ያለፈው ቅዳሜ፣እኤአ፣ጁላይ 5፣2008 በዋሽንግተን አሜሪካ የሚደረገውን ስፖርታዊ በአል አያይዞ ግንቦት 7 በጠራው ስብሰባ ላይ ቁጥሩ ከ 500 በላይ የሆነ ህዝብ መገኘቱን ስብሰባውን ይከተታል የነበረው ዘጋቢያችን ገልጾ.ከስብሰባው በሁዋላ ያነጋገራቸው ተሰብሳቢዎች በስበሰባው አካሄድ መርካታቸውንና ለግንቦት 7ም ድጋፋቸውን እንደሚሰጡ ገልጸዋል ብሏል፡፡ ስብሰባው የተደረገው በስፖርታዊ በአሉ የመዝጊያ ቀን ቢሆንም፣በርካታ ህዝብ የመዝጊያ ዝግጅቱ እና እንግዶችን መሸኘቱ ሳያግደው አዳራሹን ለማጨናነቅ እንደቻለ ተገልጿል፡፡
ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ስብሰባውን በመምራት፣አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ፣ዶ/ር ግደይ አሰፋ፣አቶ ኤፍሬም ማዴቦና አቶ ሙሉነህ ኢየኤል ተናጋሪዎች ሆነው የቀረቡ ሲሆን አቶ አንዳርጋቸው ስለ ግንቦት 7 አመሰራረትናየፖለቲካ ግብ አስረድተዋል፡፡ ዶ/ር ግደይ ደግሞ ግንቦት 7 ስለሚከተለው የትግል ስልት ትክክለኛነት ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን በንግግራቸውም፣ወያኔ በደም የተጨማለቀ ታሪክ ያለውና የከሀዲዎችና የነፍሰገዳዮች ስብስብ በመሆኑ፣ሰላማዊና የአመጽ ትግሎችን ቀላቅሎ በመታገል ማስወገድ ይገባል ብለዋል፡፡

ወደ ገጽ4 ዞሯል

# ርእሰ አንቀጽ

## የነብርን ጭራን አይይዙም ፤ ከያዙም ...

«መድረክ ለዴሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ» (መዴምኢ) የተሰኘ ስብስብ የመመሥረቱን ዜና በአንክሮ ተመልክተነዋል :: በእስር የተንገላቱ ዜጎች ፤ በግንቦት 97 ምርጫ የህዝብን ቀልብ በከፊል የሳቡ ድርጅቶች ፤ በጥቅሉ ደግሞ በህጋዊ ተቀናቃኝነት የተመዘገቡ ፓርቲዎች ፤ በዋና መልኩ በብሄረሰብ አደረጃጀት የሚያምኑ ስብስቦች ፤ በአመዛኙ በ1983ቱ የሽግግር መንግስት በባለሥልጣንነት ያገለገሉ የሃገር መሪዎች የተካተቱበት መድረክ በመሆኑ ልዩ ትኩረት ሰጥተነዋል :: ከሽግግር መንግስቱ ጅማሮ እስካሁን ለ17 አመታት በምድረ-ኢትዮጵያ ለሰፈነው ብካይ በቂ ምላሽ ይሆናል ብለን ባናምንም እንኳ ፤ በግንቦት 97 ህብረ-ብሄር የፖለቲካ ሃይሎች በምርጫው ሲያሸንፉ ፤ «በስንት መስዋእትነት ያመጣኸውን ህገ-መንግስተዊ ሥርአት የሚቀለብሱ ትምክህተኞች ተመልሰው መጡብህ» በሚል ዘረኛ ቅስቀሳ የመከላከያና የፀጥታ ሀይሉን በማስደንበር በከተሞች ብቻ ከ200 ለማያንሱ ዜጎች ፍጅት እንዲተባበሩት ማድረግ በመቻሉ ፤ አሁን የተቋቋመው የ«ምክክር መድረክ» በተመሳሳይ ክስ ሊከሰስ የማይመች በመሆኑ ፤ ሥርአቱ ከገባበት ድቀትና የመከላከያ ሃይሉም አካባቢ ከሚታየው መፍረክረክና መረበሽ አኳያ ፤ ሃገሪቱ ወዳልታሰበ ቀውስ ውስጥ እንዳትገባና ፤ መልክ ያለው ሽግግር ለማድረግ የሚረዳ ፤ የፀጥታና የመከላከያ ሃይሉ ለአመታት ከተሰገሰገበት ጠባብ ብሄርተኛ አመለካከት አንፃር ፤ በተሻለ ሊያምነው የሚችል መድረክ ሊሆን ይችላል የሚል በጎ ግምት አለን ::

ይህ በጎ ግምታችን ግን ፤ ከውስጣችን የሚመነጭ የተስፋ ድልድይ እንጂ ፤ የ«ምክክር መድረኩ»ን የመሠረቱት መሪዎች በ1983ቱ የሽግግር መንግስት ወቅት ያሳዩትን ፀረ-ኢትዮጵያዊነት ዝንባሌና አድራጎት በመርሳት አይደለም :: እኛም ይቅር ለማለት ባለን ሆደሰፊነት ፤እነርሱም ከሥልጣን በተገለሉባቸው አመታት በህዝባዊ መድረኮች ካሰሙዋቸው የፀፀት አነጋገሮች በመነሳት እንጂ :: ያወጡት መግለጫ ግልፅ እንደሚያደርገው ከሽግግር መንግስቱ እስከዛሬ ባለፉት 17 አመታት የተፈጠረውን የመለስ ክህደት እመቃና የኢትዮጵያችን ሉአላዊነት መደፈር እንዳስቆጫቸው ግልፅ ነው :: በክልል ኬላ የተሸማቀቀውን የህዝባችንን የመሥራትና የመበልፀግ መብትም በሚመለከት ያቀረቡት መፍትሄ ተገቢ ነው :: መሠረታዊ የፖለቲካ ዴሞክራሲና የነፃነት መብቶች እንዲከበሩ ያደረጉት ጥሪ የዘመኑ :: ሆኖም ሥርአቱ በሠላም እንዲለወጥ በግንቦት 1997 ሃገሬው ከአድማስ እስከ አድማስ ያደረገውን የምርጫ ንቅናቄ የሚገባውን ታሪካዊ ቦታ መግለጫው ያለማካተቱ ግን ጉልህ ቀዳዳ ሆኖ ታይቶናል :: ስለ ግንቦት የህዝባችን ዴሞክራሲያዊ ጥማት አንዳችም ቃል አለመተንፈስና ሆኖም ለ2002 ምርጫ አቅምን ለማሰባሰብ ማለም ፤ አንድም የመለስ ሥርአት በህጋዊ መንገድ በህዝብ ምርጫ ሥልጣን ላይ እንደሚገኝ ማስመሰል ፤ አለያም ለግንቦት ታሪካዊ ክንዋኔ የሚገባውን ክብደት አለመስጠት እንዳይሆን እንፈራለን :: በቀጣዮቹ ሉሎች «የምክክሩ» መግለጫዎች ዕርምቱን ለማየት ጉጉታችን ነው ::

የ«ምክክር መድረኩ» በመከላከያና የፀጥታ ሃይሎች ተአማኒ ለመሆን ካለው አቅሙም በመነጨ በሥርአቱ በጭካኔ የመወገዱም አደጋ ወለል ብሎ ይታየናል :: ምንሊክ ቤተመንግስት ውስጥ ሽብሩ እየተጧጧፈ መሆኑም ጭምጭምታው መሰማት ጀምሯል :: የ«ምክክር መድረኩ» ይፋ በተደረገ ማግስት የመለስ ማስታወቂያ ሚኒስትር ተሯሩጦ «ለግጭቶች መፈጠር መንስኤ የሆኑትን ምክንያቶች በመፍጠር ፤ መልሶ መንግስትን መክሰስ አይገባም/አይቻልም» የሚል መግለጫ ማውጣቱ የሚጠቁመውም ፤ «በትምክህተኞች መጡብህ» ሊያስደነብረው የማይችለውን የፀጥታና መከላከያ ሃይል፤ በሌሎች ክሶች ለማነሳሳት አያደባ መሆኑን ነው :: በቅንጅቱ ላይ ከደረሰው ዕመቃና ዕልቂት በበለጠ በ«ምክክር መድረኩ» መሪዎችና አባላት ላይ ሊደርስ እንደሚችል መገመት ጠንቋይ መቀለብን አይጠይቅም :: መለስ ፤ ዕንቅልፍ የሚያጣለትን ሥልጣን የበለጠ ሊነጥቁኝ ይችላሉ ብሎ ስለሚባንን :: ከግንቦት 97 ምርጫ ሁሉም መማር ያለበት ትምህርት ይሄው ነውና :: ለ«ምክክር መድረክ» መሪዎችም ያለን ምክር «የነብርን ጭራ አይይዙም .... » ነው :: በግንቦት የህዝብ ድምፅ ክፉኛ የቆሰለ ነብር በመሆኑም «የቆሰለ ነብርን ጭራ...» ማለቱም የጉዳዩን ክብደት ያሳያል እንላለን :: ለማንኛውም «የግንቦት ሰባት ንቅናቄ» ማንኛውንም የኢትዮጵያን የዴሞክራሲ ተስፋ በአንዲት ጋትም ቢሆን ወደግቡ ፊቅ የሚያደርግን የዜጎች ሙከራ ሁሉ በአድናቆት የሚቀበለው ስለሆነ ፤ የ«ምክክር መድረኩ»ንም መቋቋም በተመሳሳይ ስሜት የተቀበለው መሆኑንም መግለፅ ይወዳል ::

## “ሃገር ሳያጠፉ፣ መለስን እናጥፋ!”

ከገጽ 1 የዞረ

ፕ/ር ዳንኤል ሲናገሩ አቶ መለስ ቅንጣት የኢትዮጲያዊነት ስሜት ሳይኖራቸው ኢትዮጵያን እየገዙ መሆናቸውን ሲያስረዱ ተቆርቋሪነታቸው ለባዕዳን እንጂ ለኢትዮጵያ ያለመሆኑን አስረግጠዋል። በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸም ወንጀል፡ የሃገር ሃብት ዝርፊያና የክህደት ወነጀል እነ መለስ እየፈፀሙ ነው ያሉት ፕ/ር ዳንኤል ወደፊት ከሃገር ስለሚጠፉ ስለሚችሉ ሊያስጠጋቸው የሚችል ሃገር ይፈልጋሉ። ለዚህም ሱዳን ምቹ ሆና በማግኘታቸው 1600 ኪ.ሜ. መሬት በሚስጥር ለሱዳን እንደ ጉቦ መስጠት ነበረባቸው ብለዋል።

በእለቱ የግንቦት7 ንቅናቄን በመወከል አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ለተሰብሳቢው ባሰሙት ንግግር “እንዲህ ያሉ ክህደቶች ሲፈጸሙ በመለስ አገዛዝ የመጀመሪያው እንዳልሆኑና የተለመደ አባዜ ሲሆን፤ ሁላችንም ካልተባበርን እነዚህን ተግባራት ማስቆም እንደማንችል፣ በሃቅ ላይ የቆመ ትብብርን ስንፈጥር ብቻ ነጻነታችንንና መብታችንን የምናረጋግጥ መሆኑን አስረድተዋል:: የሃገራችን ዳር ድንበር፣ ብሄራዊ ደህንነትና ጥቅም በቋሚነት እንዲከበር፣ በእዚህ ሃገር ጥቅምና ደህንነት ላይ ወንጀል የፈጸመ መሪ በህዝብ ሊጠየቅ የሚችልበት የህዝብ የስልጣን ባለቤትነትን የግድ ይላል:: ህዘብ ስልጣን የሰጠው መንግስትና መሪ ህዝብ ከስልጣን ያነሳኛል የሚል ፈሪሃ ህዝብ ስለሚኖረው፣ መለስ ዜናዊ እንደሚያደርገው በሃገርና በህዝብ ጥቅም ላይ ወንጀል እየፈጸመ ማን ይነካኛል በሚል እብሪት በስልጣን መቀጠል አይቻለውም::”

አያይዘውም “አንድ ህዝብ ለመከራው ምንጭ የሆነን ግፈኛ አገዛዝ ስርአት በተባበረና የጋራ በሆነ ትግል ማሸነፍና በቦታው ህዝብን የስልጣን በላቤት ማድረግ ካልቻለ በየግዜው የሚነሱ አምባገነን ከሃዲዎች አገርና ህዝብ በእብሪት እንዲገሉ፣ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል” ብለዋል::

**ውድ የግንቦት 7 ልሳን አንባቢዎች፣ ለእኛ መሻሻል ይረዳ ዘንድ፣ ያላችሁን አስተያየት ፣ጥቆማ፣ መጣጥፍና**

**ሌሎችንም በዚህ ገጽ በሰፈሩት የፖስታና ኢሜይል አድራሻዎች ያድርሱን::**

**የግንቦት 7 ልሳን ዝግጅት ክፍል**

**አዘጋጆች**
ፋሲል የኔአለምና እና ደረጀ ሃ/ወልድ የቀድሞ
የአዲስ ዜና እና የነጻነት ጋዜጣ አዘጋጆች

**የፖስታ ሳጥን ቁጥር**
POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

**የግንቦት ሰባት ድምጽ ጋዜጣ የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት**
ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፣አቶ መሰፍን አማን፤አቶ ቸኮል ጌታሁን፤ሁሉም የቅንጅት ለአንድነትና ዴ ሞክራሲ ፓርቲ የላእላይ ምክር ቤት አባላት የነበሩ።

# “ደሀዎች ስንመስል፣ባለፀጋዎች ነን”

ሀብታሙ-ከአምስተርዳም

ቁመቱ ውፍረቱ፣ እጅግ ገዝፎባቸው፣
ዋርካን አንግሰውት፣ ዛፎች በላያቸው፣
ለክብሩ ሲሰግዱ፣ ከፊቱ ስር ወድቀው፣
እጅግ ሲያወድሱት፣ አለቅጥ ተጨንቀው፣
ከዕለታት አንድ ቀን፣ የተነሳው ዐውሎ፣
ዕፅዋቱን አልፎ፣ ዛፉን ሁሉ ዘሎ፣
ዋርካውን አስተኛው፣ ከስሩ መንግሎ፣
ዛፎች ደነገጡ፣ በአለቃቸው መውደቅ፣
ወደ ዋርካው ሄዱ፣ ነገሩን ለማወቅ፣
ግዝፈቱን በማየት፣ ያነገሱት ዋርካ፣
ትል የቦረቦረው፣ ባዶ ነበር ለካ።

ሰውየው፤ የንብን ቲሸርት ለብሰው ለ”ዝንብ” ሲቀሰቅሱ ያየሁዋቸው ዕለት ምሽቱን የፃፍኳት ግጥም ነች።በእርግጥም የዛሬን አያድርገውና ከነ አያሌ ጉድፋቸውም ቢሆን በሰውየው ያልማለለ ማን ነበር?በእርግጥም “የኢትዮጵያ መሪ ማነው? አል-አሙዲ?ወይስ መለስ?ብለው እስከመጠየቅ የደረሱ ስንቶች ነበሩ?”

“በምርቅዝ ቁስላችን ውስጥ ለምን እሾህ ትሰድብናለህ?”ተብዬ ካልተወቀስኩ በስተቀር፤ይህችን ግጥም የፃፍኳት ”ቆመን የሰቀልነውን ቁጭ ብለን ማውረድ አቃተን” ብለው መተረት ለጀመሩት ለቀድሞው የሰውየው አፍቃሪዎች መፅናኛ ትሆን ዘንድ ነው።

ብዙዎች፤ ሰውየውን እስከማምለክ ደርሰው የነበረው እንዲሁ በግርድፉ ”በደሀዋ አገራችን ላይ በርካታ መሰረተ-ልማቶችን ገንብተዋል፣በተሰማሩባቸው የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለዜጎች የስራ ዕድል ፈጥረዋል” ከሚልና ግራ ቀኙን ካላገናዘበ ሀሳብ በመነሳት ነበር።በሌላ አነጋገር ሰውየው፤ የኢትዮጵያንና የህዝቦቿን መከራ በማራዘም የአገሪቱን ሀብት እንደጥገት ላም ለማለብ ከገዥዎቻችን ጋር “ኒካ” ማሰራቸውን ገና በጧቱ የተገነዘብነው በጣም ጥቂቶች ነበርን።በእርግጥ በስመ-ዲሞክራሲ አምባገነናዊ መንገድን የሚከተሉ ገዥዎች፤በ”ባለሀብት ስም” እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ጋር ምስጢራዊ የጋብቻ ውል መፈፀማቸው የተለመደ ነው። የፖለቲካ ተንታኞች እንደነዚህ ዓይነቶቹንባለሀብት ተብየዎች፤”በመንግስት ውስጥ ያሉ መንግስታት (ስቴትስ ዊዝ ኢን ስቴት)”ይሏቸዋል።

የኔታ፦” ኩሉ ፃድቅ በጊዜ ርቱዕ” እንዲሉ፤እንደነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች በአገር ውስጥ የሚነፍሰው ፖለቲካዊ አየር፤ የጋብቻ ውል ላሰሩለትና ላሰረላቸው መንግስት
የሚያሰጋ ሆኖ እስካላገኙት ድረስ፤ በባለሀብት ስም ራሳቸውን ደብቀው ትንሽ ይሰራሉ፤ብዙ ይዘርፋሉ።በማንካ ሰጥተው በአካፋ ይወስዳሉ።

ጥቂቷን ግብራቸውን፤ ህዝብ በቀላሉ ሊያየውና ሊሰማው በሚችለው ነገር ላይ እንድትሆን ስለሚያደርጉም፤ ከባዱ ሸፍጥና ስርቆታቸው በጥቃቅን ነገሮች የሚዳፈንበት አጋጣሚ ይበዛል።ለትውልድ የሚበቃውን የሻኪሶን ወርቅ እያረሱ፤ አሊ ረዲን(የቡና ገበያ ጎል ጠባቂን) ደቡብ አፍሪካ ማሳከማቸውን እንደሚያስወሩት ማለት ነው።አዎ! በሁሉም ክልሎች ማለት በሚቻልበት ሁኔታ፤ በ”ልማታዊ ባለሀብት” ስም ጋሻ መሬት እየተገነደሰ ለሰውየው ሲሰጥ፤ ብዙዎች ሲያወሱ የነበረው ሰውየው ለዘፋኝ ሰርግ የሚኒባስ ጥሎሽ ስለመስጠታቸው ነበር።ዓይናችን ከአደናጋሪው የሸራተን ርችት ባሻገር ያለውን ሀቅ ማየት ባለመቻሉ፤ ርኩሱን-ቅዱስ፤ተኩላውን-በግ ስንል ከርመናል።

ስለ ሸራተኑ፣ስለ ዳሽኑ፣ስለ ሳራ አምፖሉ፣ስለ ብረታ ብረቱ፣ስለ ማምኮው፣ስለሜድሮኩ፣ሰለ ሲሚንቶው፣ስለፔፕሲ ኮላው፣ስለ አግሮ ኢንዱስትሪው፣ስለ ሰላም ነርስ ት/ቤቱ፣ስለ
ፒያሳው ግንባታ፣ስለማይከፈለው ግብር፣ስለ ብ.አ.ዴ.ኑ፣ስለ ህ.ወ.ሀ.ቱ፣ስለ ኦ.ህ.ዴ.ዱ፣ስለ ደ.ኢ.ህ.ዴ.ጉ…ወዘተ ዝርዝር ውስጥ አልገባም።

በአጭሩ ለማለት የፈለግኩት ሰውየው፤ በስመ-ነፃ ገበያ የአገሪቱን የንግድ ዘርፎች በህገ-ወጥ መንገድ ከተቆጣጠሩት ህገ-ወጥ ገዥዎቻችን ጋር በመመሳጠር፤ ከነአካቴው እያቆረቆዙን እንጅ እየሰሩልን አይደለም።በጣም ውስን የሆነው አገራዊ ሀብታችን በጥቂቶች እጅ እንደሚገኝ ‘ፒስ ፈንድ’ የተሰኘው ድርጅት ሰሞኑን ይፋ ያደረገው ጥናት ያሳያል።

“ልማታዊ ባለሀብት”በሚል ለምድ ስር ተደብቀው የአገርና የህዝብ ሀብት ሲመዘብሩ የሚኖሩት እንደዚህ ዓይነት ሰዎች፤እውነተኛ ማንነታቸው የሚገለጠው ወይም(ስቴት ዊዝ ኢን ስቴት መሆናቸው)ይፋ የሚሆነው፤በቃል ኪዳን የተሳሰሩት መንግስት ህልውና አደጋ ላይ ሲሆን ነው።ያኔ “ባለሀብት” የተሰኘው ሀሳዊ ለምድይወልቃል።የወትሮው ትህትናዊ ካባ ይገፈፋል፤ይሉኝታ “ዕንጦርጦስ ግባ!”ይባላል።የአስቴር አወቀ ሙዚቃን ሲያቀነቅን የከረመው አንደበት፤ለስድብ ይከፈታል። በሀመልማል ዘፈን እስክታ ሲል የከረመው ትከሻ ፤ለፀብ ይንጎራደዳል።ፍቅርን ሲሰብክ የከረመ አፍ፤ የበከተና የተጠላ ፖለቲካን ማነብነብ ይጀምራል።ያኔ፤ገዥውን መንግስት ከውድቀት ይታደጋል ተብሎ የታሰበ ነገር በሙሉ በደመ-ነፍስ ይደረጋል።ጊዜው ለነሱ የድንጋጤ ስለሚሆን ነው በደመ-ነፍስ ያልኩት።_ልክ ቅንጅት በምርጫው እያሸነፈ ሲመጣ ሰውየው የንብን ቲሸርት ለብሰው አደባባይ እንደውጡት ፤ወጥተውም ብዙ እንደዘላበዱት ማለት ነው።ምክንያቱም የ”ሀብታቸው”ህልውና ፤ ካለው ገዥ መንግስት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው። የምርጫውን ግርግር ተከትሎ እንዲቋቋም የተደረገው ተለጣፊ የወጣቶች ማህበርም፤ ለኢህአዴግ ይቀሰቅስ ዘንድ የተሰጠውን ተልዕኮ እንዲወጣ ፤ከሰውየው የ 2 ሚሊየን ብር ስጦታ እንደተበረከተለት ዐይተናል።የጊዮርጊስ ስፖርት ክለብን ቀስ ብለው ከተቆጣጠሩት በሁዋላ እንዴት የገዥው ፓርቲ መቀስቀሻ ሊያደርጉት እንደሞከሩና የስፖርት ቤተ-ሰቡን እንዳስቀየሙ ዐይተናል።እንግዲህ ሰሞኑን በሰሜን አሜሪካ ለሚገኘው ለኢትዮጵያውያን እግር ኳስ ማህበር የ 300 ሽህ ዶላር ስጦታ ማበርከታቸው የዚሁ ቅጥያ መሆኑ ነው-ገዥውን መንግስት የማዳን ዘመቻ።

የሰሜን አሜሪካው ስመ-ጥር የእግር የእግር ኳስ ማህበር ዝናውን፣ክብሩንና ጥንካሬውን ይዞ ለመቀጠል የሚፈልግ ከሆነ ሰሞኑን በተበረከተለት ስጦታ ዙሪያ ጉዳዩን ግራና ቀኙ ዐይቶ በአስቸኳይ ተገቢውንና ብዙሀን ኢትዮጵያውያን የሚሹትን ውሳኔ ማሳለፍ ይጠበቅበታል።እዚህ ላይ ማህበሩ ስል የማህበሩን አመራሮች ማለቴ ነው፡፡እንዲሁ ላይ ላዩን ስጦታውን መቀበል ምን አለበት?በሚል ማደናገሪያ ነገሩን አድበስብሶ ማለፍ ስህተት ይሆናል።ምክንያቱም ሰውየውን ካለፈው ታሪካቸው እንደተረዳናቸው፤ የሚያስቡት በጭንቅላታቸው ሳይሆን በገንዘባቸው ነው።የህዝብ ሀብት ወደሆነው ወደአንጋፋው የጊዮርጊስ ስፖርት ክለብ እልፍኝ፤ በእጃቸው(በብራቸው)ሰተት ብለው ከገቡ በሁዋላ ፤በክለቡ መድረክ ላይ ቅንጣት ታህል ይሉኝታ ሳይዛቸው ህዝብ የተፋውን ፖለቲካ የሰበኩ ሰው፤ዛሬ የ300 ሽህ ዶላር ማኖ ያስነኩትን ማህበር እልፍኝ፤ ነገ ጧት የፖለቲካ መፀዳጃቸው እንደማያደርጉት ምን ዋስትና አለ? ደግሞ የእግር ኳስ ማህበሩ ሀብት፣ ውበትና ታላቅነት አገር አቆራርጦ ሳይቀር በበዐሉ ለመካፈል ከያለበት የሚመጣው ብዙሀኑ ኢትዮጵያዊ እንጅ፤ዛሬ “በእጃቸው” የመጡ ሰዎች አይደሉም።ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ላይ” ለስጦታ ተብሎ” ከብዙሀኑ ፍላጎት ውጭ የሆነ ውሳኔ ማሳለፍ፤ከአራት ሰዓት በሁዋላ በእጻሪ መልክ ለሚወጣ ምስር ወጥ ብኩርናን እንደመሸጥ ነው።ደግሞም እደግመዋለሁ፤ የማህበሩ ሀብት እኛ”ሀብታሞቹ’ኢትዮጵያውያን እንጅ፤ የአዕምሮ ደሀ የሆኑ ባለ ብሮች አይደሉም።

“ደካሞች ስንመስል ሀይለኞች ነን፤ሙታን ስንባል ለሌሎች ህይወት እንሰጣለን፤ደሀዎች ስንባል ባለፀጋዎች ነን፤ምንም የሌለን ስንመስል ሁሉም የኛ ነው”ያለው ማን ነበር?

# መለስ-ሙጋቤን ደገፉ

## "ከመምህሩ-ደቀ መዝሙሩ አይበልጥም"

## "መለስ በቅርቡ የዓለማችን ቁጥር 1 አምባገነን ይሆናል" ዶክተር ብርሀኑ ነጋ

ሰሞኑን በካይሮ-ግብፅ ላይ ስብሰባ የተቀመጡትና በዚምባቡዌው ፕሬዚዳንት ላይ ጠንከር ያለ አቋም ይይዛሉ ተብለው የተጠበቁት የአፍሪካ <መሪዎች>ምንም አለማለታቸው ዓለምን እያነጋገረ ሳለ፤ይባስ ብሎ የኢትዮጵያው አምባገነን በስብሰባው ላይ ከሙጋቤ ጎን መቆማቸውን ይፋ ማድረጋቸው አስገራሚና አሰቂኝ ሆኗል። 'አጃንስ ፍራንስ ፕሬስ'፤<አፍሪካ ፉል ኦፍ ሙጋቤ> በሚል ርዕስ ባወጣው ዘገባ፤መሪዎቹ -ሮበርት ሙጋቤን ለማውገዝ ያልደፈሩት በአመዛኞቹ በዲሞክራሲያዊ መንገድ ስልጣን ላይ የወጡና ያሉ ባለመሆናቸው፤ እንዲሁም ከሙጋቤ እምብዛም የተሻለ ማንነት ስለሌላቸው መሆኑን አትቷል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፤በስብሰባው ላይ የኢትዮጵያው አምባገነን ይባስ ብሎ ለሙጋቤ ድጋፋቸውን መስጠታቸው ምዕራባውያን ታዛቢዎችን ማስገረሙ ታዎቋል።

የኢትዮጵያን ጉዳይ በቅርበት የሚከታተሉ የፖለቲካ ተንታኞች ግን፤<ይህ የሚያስገርምም፤የሚያስደነግጥም አይደለም።ይልቁንስ ይገርም የነበረው የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር-የዚምባቡዌውን ፕሬዚዳንት ባይደግፉ ነበር>ይላሉ።

እንደውም ሙጋቤ የምርጫ ውጤትን በሀይል ከመቀልበስ ጀምሮ በአሁኑ ጊዜ በ አገራቸው እየፈፀሙ ያለውን አሳፋሪ ድርጊት የተማሩት ከመለስ ዜናዊ ነው ማለት ይቻላል የሚሉት የፖለቲካ ተንታኞች፤<ከመምህሩ-ደቀ መዝሙሩ አይበልጥም፤ከመለስ-ሙጋቤ አይከፉም። አቶ መለስ-ሙጋቤን ሲደግፉ፤ ለራሳቸው መከራከራቸው ነው>በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።ዘ-ሱዳን ተሪቢዩን የተሰኘው ጋዜጣ በበኩሉ፤አቶ መለስ ለዚምባቡዌው አቻቸው ድጋፍ መስጠታቸው የማይገርም መሆኑን ጠቅሶ፤ሁለቱ የለየላቸው አምባገነኖች የሚመሳሰሉባቸውን አያሌ ባህሪያት አትቷል።

ጋዜጣው ከጠቀሳቸው የገዥዎቹ ባህሪያት መካከል፦

1-ሁለቱም አምባገነኖች መሆናቸውና የምርጫን ውጤት በሀይል መቀልበሳቸው፣

2-ይህንኑ ተከትሎ ሁለቱም የጅምላ ጭፍጨፋ እንዲፈፀም ማድረጋቸው፣

3-ሁለቱም ሚዲያውን በሞኖፖል መቆጣጠራቸውና ለነፃ ፕሬስ በር መዝጋታቸው፣

4-ሁለቱም ሲናገሩ በቋንቋ አጠቃቀማቸው <ስድ>{አሮጋንት} እና<ሀላፊነት የማይሰማቸው>{ኢሪስፖንሲብል}መሆናቸው፣

5-ሁለቱም ከአፍሪካ በርካታ የጦር ሰራዊት መሰለፋቸው፣

6-ሁለቱም በረሀብ ህዝቦችን እየጨረሱ የሚገኙ መሆናቸው

የሚሉት ይገኙበታል።

ዶክተር ብርሀኑ፤በቅርቡ በብራሰልስ ለአውሮፓ ህብረት የፓርላማ አባላት በሰጡት የምስክርነት ቃል፤<መለስ በቅርቡ ከሙጋቤ በከፋ መልኩ የዓለማችን ቁጥር አንድ አምባገነን ይሆናል>ማለታቸው አይዘነጋም።

### የግንቦት7 ታለቁ ስብሰባ ከገጽ1 የቀጠለ

ኣቶ ኤፍሬም ማዴቦ ደግሞ አሁን ስለምንገኝበት አስቸጋሪ ሁኔታ እና ስለፖለቲካ ድርጅቶች ህብረት እንዲሁም እያንዳንዱ ዜጋ ስላለበት ሀላፊነት በቂ ማብራሪያ ሰጥተዋል።በቅርቡ ከኢትዮጵያ ወደ አሜሪካ በመምጣት ግንቦት 7ትን የተቀላቀሉት አቶ ሙሉነህ በበኩላቸው በአገር ውስጥ ሰላለው አሳዛኝ እና አሰፋሪ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ሁኔታ ተናግረዋል።

አቶ ሙሉነህ፣ በአሁኑ ጊዜ ተቃዋሚዎች እንደልባቸው መንቀሳቀስ እንደማይችሉ፣ከእስር በተፈቱበት ወቅት የፈረሙት ወረቀት በመንግስት ተቋማት ላይ ተቃውሞ እንዳያደርጉ የሚያስገድድ መሆኑ፣ለፍትህ ስርአቱ ገለልተኝነት፣ለመከላከያ እና ለደህነት ሀይሉ ነጻነት እንዲሁም ስለፕሬስና ሌሎች የነጻነት ጥያቄዎች ማንሳት ወይም አንስተው ህዝቡን ለማወያየት መሞከር ወንጀል ተደርጎ እንደሚቆጠርባቸውና በምህረት የተነሳላቸው የእድሜ ልክ እስራት ተፈጻሚ እንደሚሆንባቸው ተናግረዋል። አቶ ሙሉነህ አስገዳጅ ወረቀቶችን ፈርመው ሲወጡ ታሳቢ ያደረጉት፣ በወረቀቱ ላይ የሰፈረውን እብሪትና ማስፈራሪያዎችን ተቀብለው፣ በባርነት ቀንበር ውስጥ ለመኖር ሳይሆን፣ በተፈረመው ወረቀት ላይ ለማመጽ መሆኑን ተናግረዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ ስምምነቱን ፈርሞ ከወያኔ ጋር እታገላለሁ የሚል ካለ መዘዙ ግልጽ ነው ያሉት አቶ ሙሉነህ፣ መኖር የሚቻለው መለስ ዜናዊ የሚቸረውን ልጓም እርዝመት እየጠበቁና እየተንከባከቡ ብቻ ነው ሲሉ አጠቃልለዋል።በስብሰባው የውይይት ጊዜ ግልጽ ሆነው ከወጡት ነጥቦች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

- የመለስ ዜናዊ አገዛዝ፣አፋኝ፣ገዳይ፣ አገር ሻጭ፣ከሀዲና ዘራፊ በመሆኑ ላይ ስምምነት ያለ መሆኑ
- በአገሪቱና በህዝቡ ላይ ያንዣበበው አደጋ በፖለቲካ፣በኢኮኖሚና በማህበራዊ መልኩ የሚገለጽ እና ስለችግሮቹ ብቻ ማውራት በቂ አለመሆኑ፣ቁም ነገሩ ስርአቱን እንዴት ማስወገድ ይቻላል የሚለውን መወያቱ መሆኑን
- አምባገነኑን መለስ ማስገደድ የሚቻለው የሰላማዊና የአመጽ ትግሎችን አቀናጅቶ መጓዝ ሲቻል ብቻ እንደሆነ
- ትግሉና የሚመሰረቱት ትብብሮች በግፈኛው የመለስ አገዛዝ ላይ ያነጣጠሩ መሆን እንዳለባቸው፤ የትግሉ አላማም ነጻ የሆኑ የፍትህ፣ የደህንነት፣የምርጫ ቦርድ፣ እና ሌሎች ተቋማትን መመስረት መሆኑንና

እነዚህ ተቋማት በሌሉበት ሁኔታ ምርጫ ማካሄድም ሆነ በምርጫ መሳተፍ ጨዋታ መሆኑ በስብሰባው ላይ የአብዛኛውን ድጋፍ ያገኙ እምነቶች እንደነበሩ ዘጋቢያችን ሲገልጽ የአገሪቱ የፖለቲካ እና የሲቪክ ሀይሎች በሙሉ ተመሳሳይ አቋም እንዲይዙ ማድረግ ፣ይህን ካላደረጉም ህዝብ ድጋፍ እንዲነፈጋቸው ጥሪ ተደርጓል። የግንቦት7 አላማ ስልጣን ከመያዝ ጋር የተቆራኘ ሳይሆን፣ ዲሞክራሲያዊ ስርአትን ለመገንባት ቅድሚያ ከመስጠት ጋር የተያያዘ መሆኑ፣ የህዝብ ውክልና ሳይገኝ የሚሰሩ ስራዎች በአሁኑ ጊዜ መነሳት አለባቸው ብሎ እንደማያምን፣ በመሆኑም ከስልጣን ጋር በተያያዘ በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል የሚነሳውን ውዝግብ ወደ ጎን ትቶ፣ ህዝብን የስልጣን ባለቤት ማድረግ ዋንኛ ግቡ ላደረገ ማንኛውም ዲሞክራሲያው ትብብር ዝግጁ መሆኑን በመግለጽ፣ ተሰብሳቢው ንቅናቄውን በገንዘብ፣ በጉልበት፣በእውቀት እና በሞራል ለመደገፍ ባሳየው ከፍተኛ ተነሳሽነትና በይቻላል ስሜት ተጠናቋል።

# አንተ ኩሩ ህዝብ
# አገርህን አድን !
# መብትህን አስከብር!
# ተነስ! ታገል! ተባበር!
# እንደ ቀምደቶችህ ታሪክ ስራ!